# የሞት ሞት ከዉርደትም ዉርደት

ለሰሎሞን ተካልኝና ቢጤዎቹ

ቅን ዓላማ ይዞ፣ ላመኑበት መቆም፣ በፅናት መታገል
በድል ለመወጣት፣የሚጠየቀዉን መስዋትነት መክፈል
ከእንሰሳ ለለየዉ፣ ማስተዋል ለሰጠዉ፣ ህሊና ላደለዉ
ክብር ነዉ ለሰዉ ልጅ ስምና መጠሪያዉ::
ባንፃሩ
ቀን ቆጥሮ ለማደር፣መስሎ ለመታየት
ላይገፉበት ጉዳይ፣ የኋላ የኋላ፣ ወቅት አይቶ ለመክዳት
ባደባባይ ቆሞ፣ እንደቁራ መጮህ፣ ከንቱ ጭራ መቁላት
ቅሌት ነዉ ለሰዉ ልጅ፣ የመንፈስ ባርነት
የአዕምሮ ነፃነት ሰላም የሌለበት
ከዉርደትም ዉርደት::
እራስን ከጣሉ፣ ከተንበረከኩ፣ ጥቅም አነፍንፈዉ
ዓላማን ለንዋይ፣ ስብዕናን ለገንዘብ ከሸጡ አሳልፈዉ
ዕቃ መገልገያ፣ ቁሳቁስ መሆን ነዉ፣ ለሆድ ተሸንፈዉ::

እምነት ላይቸረዉ፣ አንደበት ተግባሩ፣ ዞትር ሊጠረጠር
መቀመጫዉ ቁስል፣ እንደልብ ሳያስጮህ፣ ደፍሮ ሳይናገር
አቤት ቢል ሳይጠሩት፣ ወዴት ቢል ሳይልኩት፣
አይተዉ ሊታዘቡት፣ ሳይሰሙ ሳያምኑት
አቤት አወዳደቅ፣ ከሁለት ያጣ መሆን፣ ከዉርደትም ዉርደት::

ተንኮል ከተካነ፣ ቂም በቀል ካዘለ፣ ካሸመቀ ጠላት
ይቅር ለግዜር ሳይኖር፣ ሳይጠበቅ ምህረት
ባንድ አፍ ሁለት ምላስ ሆኖ ለመገኘት
ይጣልልኝ ብሎ፣ እንደወዶ ገባ ተልመጥምጦ መግባት
ላንዲት ከርስ፣ ላንድ ሕይወት
መሸነፍ መረታት
በወኔ መሰለብ፣ ከንቱ መኮላሸት፣ ባደባባይ መሞት
ቅሌት ነዉ ለሰዉ ልጅ፣ አጉል ሆዳምነት
አይ ዉርደት፣አይ ዉርደት

ከንጉሴ ጋማ